# በሰንደቅ ዓላማው ስር መሰባሰብና ሀገራዊ ፋይዳው

መሐሪ ይፍጠር

yiftermehari@gmail.com

በተለምዶ 'ባንዴራ' እየተባለ የሚጠራው የሀገራችን ሰንደቅ ዓላማ ለኢትዮጵያውያን እጅግ የጠለቀና የገዘፈ እንዲሁም ረቂቅ በሆነ ሁኔታ ከደማችን ጋር የሚዘዋወር ቁርኝት ያለው ብሎም እያንዳንዳችን በወልም ይሁን በተናጠል የምንታወቅበት የማንነታችን መለያና መገለጫ መሆኑ እሙን ነው፡፡ እርግጥም ከሰንደቅ ዓላማችን ጋር ተያይዘው የሚከናወኑ ማናቸውም ጉዳዮችን ስንመለት፤ ሳናውቀው ከውስጥ ስሜታችን ገንፍለው የሚወጡበት ምክንያት ይኸው ይመስለኛል፡፡ ሁላችንም እንደምናውቀው በየትውልዱ ፈረቃና ሽግግር በተለያዩ የታሪክ ዘመናትና ወቅቶች ዑደት ኢትዮጵያውያን ለሰንደቅ ዓላማቸው ክብር ሲሉ የመጨረሻውን የጀግንነት ተግባር በመፈፀም ሕይወታቸውን ቤዛ አድርገዋል፡፡



እርግጥ ነው ማንኛውም ህዝብ ሀገሩን ይወዳል። እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ግን ኢትዮጵያዊያን ለሀገራቸውና ለሰንደቅ ዓላማቸው ያላቸው ብሔራዊ ፍቅር እጅግ የተለየ ነው። ምክንያቱም ከሰንደቅ ዓላማው ጋር በተያያዘ በየጊዜው ለተለያዩ ሁነቶች የሚሰጧቸው ምላሾች ህያው ምስክሮች ናቸው፡፡ አዎ! አትሌቶቻችን በዓለም አቀፍ ውድድር እንዲሁም እግር ኳስ ተጫዋቾቻችን ሰንደቅ ዓላማችንን ይዘው ሲሰለፉና የኢትዮጵያ ስም ሲጠራ፣ እንደገናም ውድድር ገብተው ከተፎካካሪዎቻቸው ጋር ሲጋጠሙ፣ እኛም በቴሌቪዥን መስኮትም አሊያም በአካል ስንከታተል 'ተቀደምን! ወይም አሸነፍን!' እያልን እንቅልፍ አጥተን የምንጠበበው፣ የምንጨነቀውና የምንጮኸው እንዲሁም እልህና ሲቃ የሚተናነቀን ብሎም በዓለም ፊት ሁሌም አሸናፊ ሆነን መታየትን የምንመርጠው ለሰንደቅ ዓላማችን ካለን ፍቅር በመነጨ መሆኑ አያከራክርም፡፡

ለኢትዮጵያና 'ለባንዴራዋ' ያለን ጥልቅ ፍቅርና ክብር፣ የአንሸነፍም ባይነት የነደደና የተቃጠለ የሀገር ፍቅር ስሜት ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን በሀገራቸውም ሆነ በሥራ በሚኖሩባቸው የተለያዩ የዓለም ሀገራት ለሰንደቃቸው ያላቸው ፍቅር የገዘፈ ነው፡፡ የሀገራችን አትሌቶች ለውድድር በሄዱበት ሀገር የሚኖሩ ዜጎች ለእህትና ለወንድሞቻቸው በሥፍራው ተገኝተው ድጋፋቸውን ለመስጠት ሰንደቅ ዓላማቸውን ይዘው ይወጣሉ። ይጮኻሉ። ባንዲራቸውን ያውለበልባሉ፤ ያለቅሳሉም፡፡ ለዚህ ተግባራቸው ምክንያቱ ግልፅ ነው– ሰንደቅ ዓላማችን የምትወክለው ውድ ሀገራችንን፣ ኩሩውንና ጀግና ሕዝቧን ስለሆነ ነው፡፡

በ'ባንዴራችን' ውስጥ ወገናችን የሆነው ሕዝብ፣ ተወልደን ያደግንበት ቀዬ፣ ውኃ የተራጨንበት፣ ቡሄና እንቁጣጣሽ የጨፈርንበት፣ ቧርቀን ያደግንበት፣ የተማርንበት ትምህርት ቤት፣ የዕውቀትን 'ሀሁ..'ያስቆጠሩን እነ የኔታና መምሬ እንዲሁም 'አሌፍ ባታሳን...' ያስቆጠሩን እነ ሼሁ ብሎም በደስታና በሀዘን ያሳለፍናቸው ወቅቶች፣ ፍቅርና ወዳጅነት ትዝታቸው ጎልቶ ይወጣል። ከዚህ በተጨማሪም በዓል፣ ድግሱ፣ እንቁጣጣሽ፣ ገናው፣ ፋሲካው፣ አረፋውና መውሊዱ፣ የእርሻና የመኸር ወቅቱ፣ ጋራው ሸንተረሩ፣ የአርበኞችና የጀግኖች የተጋድሎ ታሪክ፣ ባህላችን፣ እምነታችን፣ ቋንቋችን፣ የማንነት መለያችን እንዲሁም በልዩነታችን ውስጥ ያለው ውብ አንድነታችን ሁሉ ይገለፃል፡፡

ይህ ብቻ አይደለም። የተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ተቻችለውና ተፈቃቅደው የሚኖሩባት፣ ከ80 በላይ ቋንቋ፣ ባህልና እምነት ባለቤት የሆነች፣ ህዝቦቿ ተከባብረውና ተሳስበው እንዲሁም በችግርም ሆነ በደስታ ብሎም በክፉ ቀን በአብሮነት የሚኖሩባት የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ልጆች መሆናችንም በሰንደቅ ዓላማው ውስጥ ይንፀባረቃል። 'ባንዴራችን' የትላንት ማንነታዊ አሻራችን መገለጫም ነው። አዎ! አፍሪካ በቅኝ ግዛት ስር በነበረችበት ወቅት ከ53 የአፍሪካ አገራት ነጻ የነበሩት ሁለት ብቻ ነበሩ። አንዷ ኢትዮጵያ ነች፡፡ ብዙዎች የአፍሪካ አገሮች ነፃ ከወጡ በኋላ የኢትዮጵያን ባንዲራ ቅጂ ለመውሰድ ሞክረዋል– ሰንደቅ ዓላማችን የነጻነትና የክብር እንዲሁም ተምሣሌት ነውና፡፡

ቀድማ በሀገሯ ላይ ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም ልብ ውስጥ የተሰቀለችና የተውለበለበች ብቸኛ ኩሩና የቀዳሚ ድል ዓርማና ምሣሌ፣ የመላው አፍሪካውያን ጌጥ ሆና የታየች ይህች የኛ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ናት፡፡ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ

እድለኛነቷም ምንጩ እዚሁ ውስጥ ያለ ነው፡፡ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በተሰማራበት አገራዊ ጉዳይ ሲነሳ ሰንደቅ ዓለማውን አስቀድሞና ከፍ አድርጎ በመያዝ ታላቅነቱን ያስታውሳል። እርግጥም ‘ታላቅ ክብር ለሰንደቅ ዓላማችን’ ሲባል፤ ጥንት፣ ትናንት፣ ዛሬም ሆነ ነገ ለኢትዮጵያ ክብርና ነጻነት ብለው ለሰንደቅ ዓላማቸው ክብር በጀግንነት ለወደቁት እንዲሁም ደማቸውን አፍስሰው አጥንታቸውን ከስክሰው እንድንኖር ላበቁን ጀግኖች አያቶቻችንና አባቶቻችን እንዲሁም ሞተው ላስከበሩን ውድ የህዝብ ልጆች ክብር ይሁን ማለት መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡ ለኢትዮጵያና ለሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ማንነት ለወደቁት ሰማዕታት ሁሉ የላቀውና የደመቀው ክብር ይድረሳቸው ማለት ጭምር መሆኑንም እንዲሁ።

አዎ! የአዲሲቷን ኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ዕውን ለማደረግ ውድ የህዝብ ልጆች ባካሄዱት እልህ አስጨራሽና መራር ትግል መተኪያ የሌለውን ህይወታቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል። በዚህም በ1988 ዓ.ም. በቁጥር 16/1988 ‘የሰንደቅ ዓላማና አርማ አዋጅ’ እንዲወጣ መሰረት ጥለዋል–ደማቸውን ዋጅተውና አጥንታቸውን ከስክሰው ሰንደቅ ዓላማውን ላስረከቡን ውድ የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ልጆች ክብርና ምስጋና ይግባቸውና። ታዲያ ይህን ዕውነታ በሚገባ የተገነዘቡት የዘመናዊቷ ኢትዮጵያ ህዝቦች የሰማዕታቱን አደራ ተቀብለው በተለይም ላለፉት 18 ዓመታት በሰንደቅ ዓላማው ጥላ ስር ተሰባስበው አያሌ ሀገራዊ ተግራትን ፈፅመዋል። ዙሪያ መለስ ዕድገትን እያስመዘገቡም ዛሬ ላይ መድረስ ችለዋል። የማንነታቸው መገለጫ በሆነው ሰንደቅ ዓላማ ስር ሆነውም ቀደም ባሉት ጊዜያት ዕለቱን በተለያዩ የሀገራችን ክልሎች አክብረዋል። ዘንድሮም ዕለቱን ለስድስተኛ ጊዜ መስከረም 13 ቀን 2006 ዓ.ም. በደማቅ ስነ-ስርዓት አክብረው ውለዋል–“ሰንደቅ ዓላማችን የብዝሃነታችን፣ የአንድነታችንንና የህዳሴያችን መገለጫ ነው” በሚል መሪ ቃል።

ታዲያ ዕለቱ ሲከበር እኔም ለውድ አንባቢዎቼ ‘በሰንደቅ ዓላማው ስር መሰባሰብና ሀገራዊ ፋይዳው’ በሚል ርዕስ ይህችን አነስተኛ መጣጥፍ እነካችሁ ልላችሁ ወደድኩ– “ያለንውን የሰጠ ንፉግ አይባልም” እንዲል ብሂሉ። እናም ከተነሳሁበት ርዕሰ-ጉዳይ አኳያ የዕለቱን መሪ ቃል ምርኩዝ በማድረግ፤ ዜጎች በሰንደቅ ዓላማው ጥላ ስር ተሰባስበው በልዩነታቸው ውስጥ ያለውን አንድነታቸውን አጠናክረው፣ ተቻችለውና ተፈቃቅደው አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ በመገንባት ረገድ ባለፉት 22 የሰላም፣ የልማትና

የዴሞክራሲ ዓመታት ያመጡትን እንዲሁም ወደፊት ሊያመጡ የሚችሉትን ሀገራዊ ፋይዳ በጥቂቱም ቢሆን ለመዳሰስ እሞክራለሁ። አብረን እንዝለቅ።…

እርግጥም ሰንደቅ ዓላማችን የብዝሃነታችን መገለጫ ነው። እንደሚታወቀው ሀገራችን የተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሁም ሃይማኖቶችና ቋንቋዎች የሚገኙባት ናት።ታዲያ ባለፉት ዓመታት ይህን ልዩነት እንደ ጥንካሬ በመውሰድ የተረጋጋየፖለቲካ ስርዓት መፍጠር የተቻለው ብሎም ብጥብጥና ሁከት ውስጥ እንዳትገባ ማድረግ የተቻለው ብዝሃነትን ማስተናገድ የሚችልና ዘለቄና ቀጣይነት ያለው ልማት ማረጋገጥ መቻሉ መሆኑ ከማንም የተሰወረ ጉዳይ አይደለም። ለዚህም ደግሞ ዋስትናው ህገ-መንግስቱ ነው። አዎ! በህገ-መንግስቱ ሳቢያ ሁሉም ዴሞክራሲያዊ መብቶች /የግልና የቡድን/ በተቀናጀ መልኩ አንዱ የሌላውን በሚደግፍ አኳኋን ተመልሰዋል። በዚህም ብዝሃነትን ለማስተናገድ ችግር የነበሩ በርካታ ጉዳዮች ሊመለሱ ችለዋል። ይህም የሀገሪቱ ልማት ላለፉት አስር ዓመታት ያለ አንዳች ሳንካ ፈጣንና ተከታታይ በሆነ መንገድ እንዲቀጥል አድርጓል።

ታዲያ እዚህ ላይ ውድ አንባቢዎቼ ይህ ሁሉን አቀፍ ሀገራዊ ትሩፋት ሊገኝ የቻለው የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በልማታዊውና ዴሞክራሲያዊው መንግስት እየተመሩ ብዝሃነታቸውን የጥንካሬያቸው ምንጭ አድርገው በሰንደቅ ዓላማው ስር ተሰባስበው ሌት ተቀን በመስራታቸው መሆኑን እንደምትገነዘቡልኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ልዩነቱን የጥንካሬው መሰረት አድርጎ በመቁጠር በ'ባንዴራው' ስር ተጠልሎ ድህነትን ለማሸነፍ ላለፉት ዓመታት ታግሏል። የውጤት ባለቤት እየሆነም ነው። ለዚያውም ከዓለም በፈጣን ዕድገት ከቻይና እና ከህንድ ቀጥሎ የልማት ተምሳሌታዊ ማማውን ጫፍ ላይ ሰቅሎ። እናም ድሉን ይበልጥ ለማጠናከር የሚችልበትን በዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድን ተልሞ ወደ መከከለኛ ገቢ የመገስገስ ራዕዩን ተያይዞታል–"ድር ቢያብር አንበሳ ያስር" እያለ። እርግጥም የብዝሃነት ድር ድህነትን እጅ ከወርች ጠፍሮ በማሰር ላይ ነው፤ የዘመናት የሃፍረት መለያ የሆነውንና ቀና ብሎ እንዳይሄድ አንገቱን ያስደፋውን ቀንደኛ ጠላቱን አምርሮ በመጥላት።

ብዙ ሆኖ በሰንደቅ ዓላማው ስር እንደ አንድ በመሰለፍ ይህን የሀገሩንና የራሱን አሉታዊ አሻራን ለመቀነስ ብሎም ህዳሴውን በቅርበት ለማየት እንደ መንደርደሪያ የሚያገለግለውን የልማት ትልም ለማሳካት ወገቡን ጠበቅ ካደረገ እነሆ ከሁለት ዓመት ተኩል በላይ ተሻግሯል። "ለብልህ አይነግሩትም" እንዲሉ በሁሉም የልማት ዘርፎች ከጫፍ

እሰከ ጫፍ በመንቀሳቀስ በ'ባንዴራው' አጊጦና አሸብርቆ የትናንት የውርደት ምንጩን ዛሬ ላይ ድል በመንሳት ወደ ፊት እየገሰገሰ ነው፤ የማይቀረውን የዕድገት ተስፋ በቅርብ ርቀት እያየ። ብዝሃነቱ የድሉ ምንጭ እንጂ የልዩነቱና የመፋለሱ ምክንያት እንዳልሆነ ላለፉት የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ዓመታት በተግባራዊ ክንዋኔው ያረጋገጠው ይህ ህዝብ፤ ነገም ይህን ጥንካሬውን አጠናክሮ በመቀጠል አጮልቆ እየተመለከተ ያለውን የብርሃን ጭላንጭል ይበልጥ ማስፋፋቱ አይቀሬ ነው፤ የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃልና።

በመሪ ቃሉ ላይ እንደተጠቆመው ሰንደቅ ዓላማችን የብዝሃነታችን መገለጫ ብቻ አይደለም– በመፈቃቀድና በመቻቻል ላይ የተመሰረተው አንድነታችን መለያ ጭምር እንጂ። ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚያውቀው፤ ኢትዮጵያ ላለፉት 18 እና 19 ዓመታት በፌዴራላዊ ስርዓት ስትተዳደር ቆይታለች። ታዲያ በእነዚህ ዓመታት ውስጥ የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች አንዱ የሌላውን ማንነት እንዲያውቅ እንዲሁም ዴሞክራሲያዊ አንድነታቸውን የሚያጠናክሩ ስራዎችን አከናውነዋል–መለያቸው በሆነው 'የባንዴራው' ታዛ ስር በመሰባሰብ። በተለይም ያለፉት ፊውዳላዊና ጨቋኝ ስርዓቶች በህዝቦች መካከል ጥለዋቸው ያለፉት ቁርሾዎችና ጠባሳዎች እንዲሽሩ፣ የመፈቀቃቀድና የወንድማማችነት መንፈስ እንዲጎለብት፣ ልዩነታቸው ተጠብቆ በሚያስተሳስሯቸው እጅግ የበዙ ታሪካዊና ነባራዊ ጉዳዩች ላይ እንዲያተኩሩ የሚያደርጉ ስራዎችን አከናውነዋል።

ይህም ተግባራቸው አንዳንድ ሟርተኞች በልዩነት ውስጥ ያለን የህዝቦችን ዴሞክራሲያዊ አንድነትን ለብተና እንደሚዳርግ በማስመሰል ያስሙ የነበሩትን ልፈፋ መና ያስቀረ ነው። እንደሚታወቀው የዛሬ 20 እና 21 ዓመታት ገደማ ሀገራችን ተበታትና ማየት የሚሹ ሃይሎች በህገ-መንግስቱ ላይ የሰፈረውን "የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብተ እስመገንጠል" የሚለውን ፍፁም ዴሞክራሲያዊ አንቀፅ ያለ ፍቺው በመጠቀም "የኢትዮጵያ ነገር አከተመለት፤ እንደ ሶማሊያና ዩጎዝላቪያ መበታተኗ አይቀረም" ሲሉ የጥንቆላ ትንበያን ሲያሰሙ ነበር። ግና ይህ ፍላጎታቸውና ሟርታቸው ሊሰምር አልቻለም። በተግባር የታየው የዚህ ተቃራኒ ነው። ከዚህ አንፃር ሁለት ተጨባጭ አብነቶችን ብቻ ላንሳ–በአምባገነኑ የኤርትራ መንግስት ወረራ እና በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ወቅቶች የታዩትን ከብረት የጠነከሩ የአንድነት ተምሳሌቶችን።

ሻዕቢያ በድንበር ይገባኛል ሽፋን በሌሎች ሀገራት አንጡራ ሀብት ላይ ተንጠላጥሎ ለማደግ የነበረው የጥገኝነት ፍላጐቱ ሲከሽፍበት “ኢትዮጵያውያን ተከፋፍለዋል፣ አንድነት የላቸውም” በሚል የተሳሳተ ምልከታ በቀጥታ ያመራው ባድመንና አካባቢውን ወደ መውረር እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው፡፡ ታዲያ በወቅቱ ሁሉም የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሰንደቅ ዓላማቸውን በማንገብ ቀፎው እንደተነካ ንብ ‘ሆ!’ ብለው በመነሣት የሀገሪቱን ሉዓላዊነት በመስዕዋትነታቸው ለማስከበር ያላቸውን ቁርጠኝነት በመግለፅ አፋጣኝ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ የሠራዊታችንን ክንድ ለማፈርጠም ይቻል ዘንድም ልጆቻቸውን ወደ የማሰልጠኛዎች እንዲከቱ አድርገዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ግንባር ድረስ እየተገኙ ገንዘብና ቁሳቁስ በመለገስ ለሀገራቸው ዳር ድንበር መከበር በፍፁም ኢትዮጵያዊ አንድነትን በተላበሰ ስሜት ድጋፍ ማድረጋቸው አይዘነጋም። ታዲያ እነዚህን ሁሉ ተግባራት ሲከውኑ በአንድ እጃቸው በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድነታቸውን የሚገልፁበትን ድጋፋቸውን፣ በሌላኛው ደግሞ ሰንደቅ ዓላማቸውን ይዘው ነው። ከዚህም ‘ባንዴራችን’ የሉዓላዊነታችን መሰባሰቢያ አፀድ መሆኑን በቀላሉ ለመገንዘብ አያዳግትም።

ሁላችንም እንደምንገነዘበው በልዩነታችን ውስጥ ያለውን አንድነታችንን ዳግም ከጠበቁት ዘመን አይሽሬ ክስተቶች መካከል በታላቁ መሪያችን በአቶ መለስ ዜናዊና በድርጅታቸው አማካኝነት የተተለመው የህዳሴው ግድብ ግንባታ ብስራት- ዜና መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡ ዘር ፣እምነት፣ ቋንቋና የፖለቲካ ልዩነት ሳይገድበው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ያለምንም ተቃውሞና ድምፀ- ተዓቅቦ ሰንደቅ ዓላማው ስር ተሰባስቦ በአንድ ድምፅ አፅድቆታል፡፡

ታዲያ እዚህ ላይ የዘመን ቁጭታችንን ያረገበው ይህ ታላቅ ፕሮጀክት ዕውን እንዲሆን መላው ኢትዮጵያዊ በአንድ ድምፅ የተቀበለው እንዲሁ ዝም ብሎ አይደለም– በመፈቃድ ላይ ከተመሰረተው ዴሞክራሲያዊ አንድነቱ በመነሳት ከልብ ከመነጨ ስሜት ያሳየው ሀገራዊ ፍቅር እንጂ፡፡ ታዲያ ለግንባታው ሁሉም እንደየ አቅሙ በጉልበቱ፣ በዕውቀቱ፣ በገንዘቡ የሚጠበቅበትንና ከሚጠበቅበትም በላይ የዜግነቱን ለማበርከት ቃል ገብቶ፣ ቃሉንም በተግባር መለወጥ መቻሉን ማስታወስ ብቻ በቂ ይመስለኛል። ለምን ቢባል ለአንድነታችን መገለጫ ይህን ከመሰለው ምግባር የቀደመ ታማኝ እማኝ ሊኖር ስለማይችል ነው። አዎ! ኢትዮጵያዊ ሁሉ ለግድቡ ግንባታ የሰጠውና አሁንም ያለማቋረጥ እየሰጠ ያለው ምላሽ እርግጥም በታሪክ ድርሳን ተከትቦ መቀመጥ ያለበት ነው፡፡

ምክንያቱም የ‘ባንዴራው’ ሃይል ምን ያህል እንዳስተሳሰረንና እንዴት የዴሞክራሲያዊ አንድነታችን ማህተም እንደሆነ ያለመስካሪ ራሱ ሊናገር ስለሚችል ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ የ“ይበታተናሉ” ሟርተኞችን ቅዠትና ውትወታ የቁራ ጩኸት አድርጓል።

እርግጥ እዚህ ላይ ስለ ሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ አንድነት ሲነሳ፤ ጉዳዩ አንድነት ፈጣን ልማትንና የጋራ ተጠቃሚነትን ከማስገኘት አኳያ ያለው ፋይዳም ከግምት ውስጥ እንደሚገባ መረዳት ያስፈልጋል። በቡድንም ይሁን በሀገር ደረጃ ያለ አንድነት የሚከናወን ነገር የለም። አንድነት ሲኖር ፈጣን ልማትና የተሻለ አቅም መፍጠር ይቻላል። አዎ! አንድነት ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የህዝቦች ሁሉን አቀፍ ተጠቃሚነት ሊያረጋግጥ የሚችለው እኩልነትና መፈቃቀድ ሲኖር ነው። የሀገራችን ህዝቦች አንድነት ህገ-መንግስታዊ መሰረት ያለው እንዲሁም የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ዕኑ ፍላጎትንና እምነትን መሰረት ያደረገ ነው። የዚህ ዕውነታ ነፀብራቅ መሰባሰቢያ ጥላ ደግሞ ‘ባንዴራው’ መሆኑ አይካድም። እናም ሰንደቅ ዓላማችን ህዝቦች ይህን ዴሞክራሲያዊ አንድነትን ጠብቀው የጋራ ተጠቃሚነታቸውን ለማጎልበት ጉልህ ሚና እንዳለው መገንዘብ ያስፈልጋል ባይ ነኝ።

ይህ ብቻም አይደለም። ሰንደቅ ዓላማችን የህዳሴያችን መሰረትም ጭምር ነው። ሁላችንም እንደምንገነዘበው የሀገራችን ህዳሴ ራዕይ “በህዝብ ተሳትፎና መፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትና መልካም አስተዳደር የሰፈነባት፣ ማህበራዊ ፍትህ የነገሰባት ከድህነት ተላቃ መካከለኛ ገቢ ያላት ኢትዮጵያን ዕውን ማድረግ ነው” መሆኑ ከማንም የተሰወረ ጉዳይ አይደለም። ከዚህ አኳያ ሀገራችን በምጣኔ-ሃብት እንድታድግ፣ የዜጎችን ሁለንተናዊ ዕድገት ተጠቃሚነት እንዲጎለብት፣ የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ባህል ግንባታ ስር እንዲሰድ ብሎም በርካታ ተግባራት ገቢራዊ ሆነው ውጤት ተገኝቶባቸዋል። ለዚህም የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች እኩልነትና ፍትህ መረጋገጥ ቁልፍ ሚና ተጫውቷል።

ለነገሩ ይህ እኩልነትንና ፍትህን በማጣጣም ላይ የሚገኘው የሀገራችን ህዝብ አሁን ካለበት “እሱነቱ” መላቀቅና መለወጥ አይፈልግም ተብሎ አይታሰብም፡፡ ምክንያቱም የቀደምት አበውንና እመውን የስልጣኔ ማንነት እየተመለከተ፣ የሀገሩን የድህነትና የኋላ ቀርነት ግርዶሽን በመቅደድ ወደ አዲስ ማንነቱ ተቀይሮ ለመታደስ የማይፈልግ ዜጋ አለ ብሎ መገመትም የዋህነት ነው፡፡ ‘ትላንት በስልጣኔ ማማ ላይ የነበረች ሀገሬ፣ ዛሬ በእኔ

ትውልድ እንደምን የረሃብ ተምሳሌት ሆና ትጠቀሳለች?' በሚል ቁጭትም፤ የነገ "እሱነቱን" እውን ለማድረግ መታተሩ የግድ መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡

ታዲያ ይህን ለመከወን በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ደግሞ በታላቁ መሪያችን አቶ መለስ ዜናዊ የተጀመረውና ዛሬ በልማታዊውና ዴሞክራሲያዊው መንግስት አማካኝነት የቀጠለውና ወደ ነበርንበት የስልጣኔ በር የሚያዘልቀን የህዳሴ መንገድ ተጀምሯል፡፡ ቀደም ሲል የጠቀስኩት የአንድነታችን ማሳያ የሆነው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ወደዚህ በር የሚደረገው ቁርጠኛ ጉዞ አንድ ማሳያ ነው ማለት ይቻላል፡፡

እርግጥ ባለፉት ዓመታት ለህዳሴው ጉዞ ምቹ መደላድል የሚፈጥሩ ስኬታማ ተግባራትን በብዙ እጥፍ በማስፋፋት ድህነትን ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ በተደረገው ርብርብ መላው የሀገራችን ህዝቦች ወደ አዲስ ስልጣኔ ለመትመም ተሳትፏቸው እየጎለበተ መጥቷል። ታዲያ በዚህ አዲስ የስልጣኔ ጉዟቸው ሁሉም ህዝቦች እምነታቸውን ጠብቀው፣ ባህላቸውንና ቋንቋቸውን አክብረው ብሎም ልዩነታቸውን አቻችለው የጋራ ተጠቃሚነታቸውን ይበልጥ የሚያሳድጉበት አዲስ አቅጣጫ ቀይሰው እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ። እናም ይህን ረጅም፣ ነገር ግን የሚሳካ የህዳሴ ጉዞ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ መጀመራቸው ሀገራችን በውጤት ላይ ውጤት የተደረበ ፈጣንና ተከታታይ ዕድገት እንድታስመዘግብ አድርገዋታል።

እርግጥ አንዳንድ ወገኖች የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ በጣም የተለጠጠ በመሆኑ ሊሳካ እንደማይችል በየጊዜው ቢወተውቱም፤ በሰንደቅ ዓላማው ስር የተሰባሰበውና የሀገሩን መፃዒ ተስፋ ድል ላይ ሆኖ አሻግሮ የሚመለከተው የሀገራችን ህዝብ ግን እስካሁን ድረስ ባከናወናቸው ተግባራት የማይታበዩ ስኬቶችን አስመዝግቧል። አዎ! የዕቅዱ ፍሬያማነት ከወዲሁ እየተመዘገበና እየተመሰከረ ነው፡፡ ለነገሩ ዕቅዱ ለስኬት እየበቃ ያለው ቀላል ስለሆነ አይደለም፡፡ ይልቁንም ግዙፍና መልከ ብዙ ፕሮጀክቶችን ያቀፈ ነው። ዳሩ ግን የዕቅዱ ክፍሎች የቱንም ያህል የገዘፉና የማይሞከሩ ቢመስሉም፤ መንግስት ወትሮም ወደ ስራ የተገባው የህዝቡን ይሁንታ አግኝቶና በጥናት ተደግፎ ስለነበር ስኬታማነቱ የሚያጠራጥር አልነበርም፡፡ መንግስት ስለ ዕቅዱ ስኬታማነት እርግጠኛ ሆኖ ከዛሬ ሁለት ዓመት ተኩል በፊት ወደ ትግበራ በገባበት ወቅት፣ በዋነኛነት የተማመነው በህዝቡ ነበር፡፡

ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚገነዘበው ሀገራችንን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለማሰለፍና ከድህነት ተምሳሌትነት ለማውጣት የምንችለው ጠንክረንና በትልቁ አቅደን በመስራት እንጂ ገና ለገና የተለጠጠ ዕቅድን በመፍራት አይደለም፡፡ ህዝቡም ሆነ መንግስት በአንድ ቋንቋ እንደሚሉት፤ ልክ እንደ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ወገብ የሚያጎብጡ፣ ነገር ግን በሃፍረት የተደፉ አንገታችንን ቀና ማድረግ የሚችሉ ግዙፍ ፕሮጀክቶችን መቀመር አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው—የሞት ሽረት ትንቅንቅ ነውና። ይህ ካልሆነ የምንፈልጋት አዲስ ኢትዮጵያ፣ ህዝቦቿ ከድህነት አረንቋ የወጡባት ሀገር ልትፈጠር አትችልም – አለመፈጠር ብቻም ሳይሆን እንደ ሀገርና ህዝብ የመኖር ህልውናችን በመስቀለኛ መንገድ ላይ ሊቆም የሚችል አይመስለኝም፡፡

ግና እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ሀገራችን በእስካሁን ጉዞዋ ያስመዘገበቻቸው የልማት፣ የሠላምና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባህል ግንባታ ትሩፋቶች ለህዝቧ ብርታት ሆነዋል። ትላንት ከዛሬው የላቀ መስራት እንደምችል ትምህርት ሰጥቶናል፡፡ እናም ምንም እንኳን በትላንት አጥጋቢ ድሎቻችን እየተመጻደቅን ዛሬን በማባከን ነገን ከመስራት የምንቦዝን ባንሆንም፣ ባለ ተስፋ መሆናችንን ግን ቢያንስ በእጆቻችን በገቡ የልማት ድሎች ልበ ሙሉዎች ብንሆን ተገቢ ነው—ብልህነት ነውና። ብልህነት በትልቁ አቅዶ በትልቁ መስራት እንጂ በትንሹ አቅዶ በትንሹ መስራት አይደለም፤ የትም አያደርስምና፡፡ ለነገሩስ “ትልቅ ተመኝ፣ ትልቅ እንድታገኝ” ይባል የለ?– እርግጥም ትልቅ ተመኝተን ትልቅ እያገኘን ነው፤ የታላቆች ታላቅም ልንሆን ነው፡፡

እንደሚታወቀው ሀገራችን ከግብርና መር ኢኮኖሚ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለመሸጋገር አቅዳና ከህዝቧ ጋር መክራ ሌት ተቀን እየሰራች ነው፡፡ እንግዲህ ይህን የኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ሥርዓት የማሳለጥና ለቀጣይ ልማታችን ምቹ መደላድል ለመፍጠር ነው– ኢትዮጵያ ግዙፍና የማይሞከሩ ፕሮጀክቶችን ነድፋ በተግባር መንቀሳቀስ የጀመረችው፤ ውጤት ማስመዝገብም የቻለችው፡፡ ከዓመታት በኋላ በኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ የሚተካውን የግብርናውን ዘርፍ በ15 በመቶ ለማሳደግ ዕቅድ ተይዟል፡፡ ታዲያ ይህን ያህል ወገብ የሚያጎብጥ ዕቅድን ለማሳካት እንዲሁም ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር መንግስትና ህዝብ መክረው ወደ ተግባር ሲገቡ፤ አንድም ቀደም ያሉ ተከታታይና ፈጣን ዕድገት በመቀመር አሊያም የአፈጻጸም ችግሮችን በመቅረፍ የሲቪል ሰርቪስ ሥርዓቱን ይበልጥ ለማዘመን ነው፡፡ በዚህም መሰረት ዛሬ ዘመናዊ የግብርና

ማዕከላት ተስፋፍተዋል፤ እየተስፋፉም ነው፡፡ ትላልቅ ፋብሪካዎችና ኢንዱስትሪዎች ተገንብተዋል፤ በመገንባት ላይም ይገኛሉ።

ሁላችንም እንደምንገነዘበው ለፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት የመሰረተ- ልማት መስክ በደም ስርነት ይመሰላል፡፡ ይህን የልማት ዋነኛ ዘርፍ ለማዘመን ዘመናዊ መንገዶች እየተገነቡ ነው፡፡ ተገንብተዋልም፡፡ በተለይም ከግብርናው ምርት እመርታ ጋር ምርታማነቱ አብሮ የሚያሻቅበውን ሸቀጥ ለማጓጓዝ የባቡር ትራንስፖርት ወሳኝ ድርሻ ያለው በመሆኑ፤ በኤሌክትሪክ የሚሰራ ዘመናዊ የባቡር መስመር ዝርጋታው ተጀምሯል፡፡ ስራውም አጓጊ እየሆነ ነው። የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትም እየተሳለጠ ነው፡፡ በታዳሽ ምንጮች በተለይም በግድቦች ግንባታ ከ6 ሺህ እስከ 8 ሺህ ሜጋ ዋት ድረስ በማመንጨት በድምሩ እስከ 10 ሺህ ሜጋ ዋት የመብራት ኃይል የማመንጨት ስራው ተጧጡፏል። በምድረ አፍሪካ በቴሌኮሙኒኬሽን ዝማኔ ግንባር ቀደም ከሚባሉት ግብጽና ደቡብ አፍሪካ ጋር የሚወዳደር የመረጃ መረብ (Internet) እንዲኖረንና ከ40 ሚሊዮን የሞባይል ተንቀሳቃሽ ስልክ ተገልጋይ እንዲሆን ለማድረግ ታቅዶ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡ ስራውም ውጤት እያስገኘ ነው።

በትምህርቱ ዘርፍ በኩልም ቢሆን ከታቀደው በበለጠ ስኬቶችን ለማስመዝገብ ተችሏል፡፡ በአንደኛና ሁለተኛ እንዲሁም በመሰናዶ ብሎም በቴክኒክና ሙያ ዘርፎች አጥጋቢ ውጤቶች እየተገኙ ነው። ጥራቱን የጠበቀ የመደበኛና ዘመናዊ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በአራቱም የሀገራችን አቅጣጫዎች እየተስፋፉ ነው፡፡ እርግጥ ጊዜና ቦታ ስለሚገድቡኝ እንጂ ሌሎቹንም የዕቅዱን ስኬቶች በሙሉ መዘርዘር ይቻል ነበር። ይሁንና እነዚህ የየዘርፉ ክንዋኔዎች ጉልህ ማሳያዎች በመሆናቸው የሌሎቹን ወጤቶችን በእነዚሁ የልማት እመርታዎች መነፅር ውስጥ ማየት ይቻላል።

ያም ሆነ ይህ ግን እነዚህ ስኬቶች መንግስት የአምስት ዓመቱን የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዕውን በማድረግ ዜጎችን የተሻለ ኑሮ እንዲኖሩ እንዲሁም ሀገራችንን ከድህነት ለማላቀቅ መሻቱ እርግጥም ከምንም ተነስቶ እንዳልነበር የሚያመላክቱ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ባቀዳቸው የተጠኑና የተቀመሩ ስልቶች ውስጥ ህዝቡ የሚኖረውን የማይተካ ሚና ተማምኖ እንዲሁም ካለፈው የዕድገት ውጤታማነት ተሞክሮው የልማት ትልሙ ገቢራዊ እንደሚሆን ስላወቀ ነው፡፡ ይህ እምነቱም ነገንም የሚያካትት ነው። አዎ! በቀሪዎቹ የዕቅዱ ዓመታት ወደ ነገው ተስፋችን የምንወጣበትን ማማ አጥብቀን ስለምንይዝ

ይበልጥ ወደ ተሻለ የዕድገት ከፍታ ላይ መረማመዳች አይቀሬ ነው፡፡ ይህን ሁሉ ሀገራዊ ፋይዳ የምንከውነው ደግሞ በ'ባንዴራችን' ስር ተሰባስበን መሆኑ መቼም ቢሆን መዘንጋት የለበትም። እናም ሁሌም "ክብር ለሰንደቅ ዓላማችን" ማለት ይገባናል። አበቃሁ።